# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

## የስኬት መንገዶችን ቀያሹ የኮርፖሬት ፕላኒንግ ዘርፍ

ተቋማት ሲፈጠሩ ወይም ሲደራጁ የየራሳቸው የሆኑ ተልዕኮዎች አሏቸው። ተልዕኮ ሲባል ደግሞ አንድን ተግባር ምን እንደሆነ የሚያመላክት፣ ራዕይን እንዴት ማሳካትና ወደ መዳረሻ እንዴት መጓዝ እንደሚቻል የሚያሳይ ፈር ቀያሽ እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ። የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይልም ታዳሽ ኃይል ላይ ትኩረት በማድረግ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማከፋፈያ መሠረተ ልማቶችን የአዋጭነት፣ የቅየሳ፣ የዲዛይን፣ የመገንባት፣ የማሻሻል፣ የመጠገን እና የማስተዳደር ተግባራትን ማከናወን፤ ኤሌክትሪክ በጅምላ በመሸጥና በመግዛት ለሀገር ብልጽግናና ለአህጉራዊ ትስስር መሠረት የሚሆን አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ የኤሌክትሪክ ኃይል ማቅረብ በሚል ተልዕኮ የተቋቋመ መንግሥታዊ የልማት ድርጅት ነው።

እንደምን ሰነበታችሁ ወድ አንባቢያን! በዛሬው ጽfከፋችን ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ውጤታማነት ጀርባ ጉልህ ድርሻ ከሚጫወቱ የሥራ ክፍሎች አንዱ ስለሆነው እና የተቋሙ አጠቃላይ የሥራ ሂደቶች ስለሚመሩበት ዕቅድ (corporate planning) ዘርፍ የምናስቃናችሁ ይሆናል። የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ግዙፍ በጀት ተመድቦላቸው ትልልቅ ፕሮጀክቶችን ከሚገነቡ እና ከፍተኛ የሰው ኃይል ከሚያስተዳድሩ ተቋማት አንዱ እንደሆነ ቀደም ሲል ማንሳታችን ይታወሳል።

ይህን ግዙፍ ኢኮኖሚ፣ ፕሮጀክትና የሰው ኃይል አስተባብሮና አጣጥሞ ውጤታማ መሆን የተቻለው እያንዳንዱ ሥራ በዕቅድ ስለሚመራ ነው። የተቋሙ ሥራዎች በታቀደላቸው ጊዜ ተጀምረው አስከሚጠናቀቁ ድረስ ከዕቅድ ማውጣት ጀምሮ የክትትልና የደጋፍ ሥራዎችን በመሥራት ኃላፊነቱን


አቶ አንዷለም ሲአ

እየተወጣ ያለው ደግሞ የኮርፖሬት ፕላኒንግ ዘርፍ ነው።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮርፖሬት ፕላኒንግ ዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ አቶ አንዷለም ሲአ እንደሚናገሩት፤

የኮርፖሬት ፕላኒንግ ዘርፍ የተቋሙን ዋና ዕቅድ የሚያዘጋጅ፣ አተገባበሩን ወይም አፈጻጸሙን የሚከታተል፣ በየጊዜው በሚገኙ ውጤቶች ላይ ተመርኩዞ ተጨማሪ ማስተካከያዎችንና ማሻሻያዎችን የሚያደርግ፣ ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ በሚገባ እንዲወጣ እያንዳንዱ ፈጻሚ አካል ትክክለኛውን አቅጣጫ እንዲከተል የሚያስችል ዘርፍ ነው።

ተቋም ካለ ዕቅድ «መሪ የሌለው መኪና ነው» ያሉት አቶ አንዷለም፤ አንድ መኪና በተፈቀደለት መንገድ ካልተጓዘ መጨረሻው መጥፋት እንደሆነው ሁሉ ለአንድ ተቋም ተልዕኮ መሳካት ወይም በሕይወት መቆየት ዕቅድ አስፈላጊ መሆኑን አብራርተዋል።

ዘርፉ ተቋሙ የሚያከናውናቸውን ዕቅዶችን የሚያዘጋጅ ሲሆን ለዚህም ተልዕኮ መሳካት በሥሩ ስድስት መምሪያዎችን አደራጅቷል። ከእነዚህ ውስጥ የመጀመሪያው ስትራቴጂክና ኢንቨስትመንት መምሪያ ነው። ይህ መምሪያ በኃይል ማመንጫዎችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች እንዲሁም ማስተላለፊያ መስመሮች ያሉ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅዶችን ስትራቴጂክ በሆነ መልኩ የሚቃኝ፣ ኢንቨስትመንቶች አዋጭና ዘላቂ በሆነ መልኩ ወጪን መልሰው አትራፊ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው።

ሁለተኛው የፓዎር ሲስተም ዕቅድ መምሪያ ነው። ይህ መምሪያ የአንድን ፕሮጀክት አስፈላጊነት በጥልቀት በማየትና በመገምገም ከቴክኒክ አንጻር እንዴት ሊተገበር ይችላል? የትኛውን ከየትኛው ብናገናኝ አዋጭ ሊሆን ይችላል? ምን ምን ጉዳዮች ያስፈልጉታል? የሚሉትን በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ አጎልብቶና አልምቶ የቀረበው ጉዳይ ያስኬዳል ወይስ አያስኬድም? በሚል ካረጋገጠ በኋላ ወደ ዲዛይን እንዲሸጋገር የሚያደርግ ነው።

ሦስተኛው የአካባቢ፣ የጤና እና የማህበራዊ ጉዳዮች መምሪያ ነው። ይህ ዘርፍ የሚገነቡት ፕሮጀክቶች በአካባቢው ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ? ወይም አካባቢው በፕሮጀቶቹ ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል? በቦታው ላይ ሠራተኞች ሲሰማሩ ጤናቸውን የሚያውክ ነገር ምንድን ነው? ማሕበረሰቡ ፕሮጀክቱን እንደራሱ ንብረት የመንከባከብ አቅሙና ፍላጎቱ ምን ይመስላል? ፕሮጀክቱ በአካባቢው ነዋሪ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ወይም የሚያበረክተው ጥቅም ምንድን ነው? የሚሉትን ይተነትናል።

አራተኛው መምሪያ ሁሉንም የቴክኒካል ጉዳዮች በማየትና በመደመር የአካባቢና የማህበራዊ ጉዳዮች ያላቸውን ተፅዕኖ ከተመለከተ በኋላ ምን አደጋ ሊያጋጥም ይችላል? ከኢኮኖሚ እና ከፋይናንስ አንጻር ምን ዓይነት ሁኔታ ይኖራል? አደጋዎቹን በምን ዓይነት ሁኔታ መቆጣጠር ይቻላል? ተጽዕኗቸውን እንዴት ማስወገድ ይቻላል? በማለት የኢኮኖሚና የፋይናንስ እንዲሁም የአደጋ ትንተና የሚሠራ ዘርፍ ነው።

አምስተኛው የዕቅድ ክትትልና ግምገማ መምሪያ ሲሆን ይህም በተቋሙ ውስጥ ያሉ ሁሉም ዘርፎች በምን ዓይነት መንገድ ዕቅዱን እየተገበሩት እንዳሉ እና የተቋሙን ድምር ውጤት የሚይይ ዘርፍ ነው። ዕቅዶቹ በታሰበው መንገድ ውጤት እያመጡ ነው? የሚለውን ካጠና በኋላ የማሻሻያ ርምጃዎችን በመውሰድ ለስትራቴጂና ለኢንቨስትመንት ለቀጣይ ግብዓት መሆን የሚችሉ መረጃዎችን ይሰጣል።

ስድስተኛውና የመጨረሻው የምርምርና ልህቀት መምሪያ ነው። ይህ መምሪያ በሥራ ላይ ያሉ አሠራሮችን፣ ቴክኖሎጂዎችና ግብዓቶችን ችግር መለየትና ምርምሮችን ማድረግ እንዲሁም ለችግሮቹ መፍትሄ የሚሰጥ ነው። እንደሚታወቀው ለኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት የሚውሉ ቴክኖሊጂዎችና ግብዓቶች በብዛት የሚመጡት ከውጭ አገር ነው። ቴክኖሎጂዎቹ ዲዛይን የሚደረጉትም በተለያዩ የዓለም አገራት እንዲተገበሩ ታስቦ እንደሆነ የተናገሩት አቶ አንዷለም፤ ግብዓቶቹ ለኢትዮጵያ ተብለው ስለማይዘጋጁ ጥቅም ላይ ለማዋል ሲታሰብ የሚጎድላቸው ነገር ሊኖር ይችላል።

ስለሆነም መምሪያው ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብዓቶችንና ቴክኖሎጂዎችን የማላመድ "Adaptation" ሥራዎችን የሚሠራ ሲሆን የማላመድ ሥራ በመመሪያው ውስጥ በታቀፉ ሙያተኞች የራስ አቅም የሚከናወን ነው። መመሪያው ከዚህ ተልዕኮው በተጨማሪ በተቋሙና በዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም በኢነርጂ ሴክተሮች መካከል ድልድይ ሆኖ ያገለግላል። ለዛሬ በዚሁ እናብቃ! በቀጣይ የዘርፉን ዝርዝር የሥራ ክንውኖች እና ውጤቶች በተመለከተ የምናስነብባችሁ ይሆናል። እስከዚያው ቸር እንሰንብት።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል